VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH

# በ2023 በበልግ እና ክረምት (FALL & WINTER) የሚሰጡ ክትባቶች

| ክትባት | ስለ ክትባቱ | ማን ሊያገኘው (ሊከተበው) ይችላል | ለምን ማግኘት እንደሚገባ | መቼ ማግኘት እንደሚቻል | የት ማግኘት እንደሚቻል |
|---|---|---|---|---|---|
| **የጉንፋን ክትባት** | አመታዊ የጉንፋን (የፍሉ) ክትባት በዚህ የጉንፋን ወቅት በጣም የተለመዱ ሆነው የሚገመቱ 4ቱን የጉንፋን ቫይረሶች ለመከላከል የተዘጋጀ ነው። | እድሜው 6 ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆነ እያንዳንዱ ሰው። | ክትባቱ የጉንፋን ህመምን፣ ሆስፒታል መተኛትን እና የመሞት አደጋን ሊቀንስ ይችላል። ጉንፋን ለያዛቸው ሰዎች፣ የህመሙን የክብደት መጠን ሊቀንስ ይችላል። | ሴፕቴምበር እና ኦክቶበር ላይ ክትባቱን ማግኘት በጣም ጥሩ ጊዜ ነው፣ ነገር ግን በኋላ ላይ ከተወሰደ እና ጉንፋኑ እየተዘዋወረ እያለ እንኳን ቢሆን ጥበቃን ያደርጋል። | የጤና መምሪያዎች፣ ፋርማሲዎች እና የህክምና ጽህፈት ቤቶች። በvaccinate.virginia.gov ላይ መገኛ ቦታን ፈልገው ያግኙ |
| **የኮቪድ-19 ክትባት** | የ2023–2024 የኮቪድ-19 ክትባቶች የOmicron XBB.1.5 ዝርያን ኢላማ ለማድረግ ዘምነዋል (ተሻሽለዋል) እንዲሁም ከሌሎች የOmicron ዝርያዎች ጥበቃን እንደሚሰጡ ይጠበቃል። | እድሜው 6 ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆነ እያንዳንዱ ሰው። | የቅርብ ጊዜ የኮቪድ-19 ክትባቶችን በመከታተል ላይ ሆኖ መቆየት በኮቪድ-19 ምክንያት በጠና ህመም ከመታመም፣ ሆስፒታል ከመተኛት እና ከሞት ይከላከላል። እንዲሁም በኮቪድ ከመያዝ በኋላ እንደገና በበሽታው የመያዝ / በሽታው የመቀጠል (Long COVID) አደጋን ይቀንሳል። | ሰዎች አሁን ላይ ክትባት ማግኘት ይችላሉ። ለኮቪድ-19 አስቀድመው ክትባት የወሰዱ ሰዎች የመጨረሻ ዶዝ (መጠን) ከወሰዱ ቢያንስ ከ2 ወራት በኋላ ክትባቱን ማግኘት ይቻላል። | የጤና መምሪያዎች፣ ፋርማሲዎች እና የህክምና ጽህፈት ቤቶች። በvaccinate.virginia.gov ላይ መገኛ ቦታን ያግኙ |
| **የRSV ክትባት በእድሜ ለገፉ አዋቂዎች** | ከባድ RSVን ለመከላከል 60 አመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆናቸው አዋቂ ሰዎች አዲስ ክትባት። | ከዶክተራቸው ጋር ምክክር በማድረግ 60 አመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆናቸው አዋቂ ሰዎች። | ዕድሜያቸው 60 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አዋቂዎች እና ሥር የሰደደ የጤና እክል ያለባቸው አዋቂዎች ከRSV ለሚመጣ ከባድ ሕመም፣ በሆስፒታል መተኛት ወይም ሞት የተጋለጡ ናቸው። | ሴፕቴምበር እና ኦክቶበር ላይ ክትባቱን ማግኘት በጣም ጥሩ ጊዜ ነው፣ ነገር ግን በኋላ ላይ በRSV ወቅት ከተወሰደ አሁንም ጥበቃን ሊያደርግ ይችላል። | የጤና መምሪያዎች፣ ፋርማሲዎች እና የህክምና ጽህፈት ቤቶች። |
| **RSV ክትባት ለነፍሰ ጡር ሰዎች** | ነፍሰ ጡር ሰዎች ጨቅላ ልጆቻቸውን በመጀመሪያ 6 ወራት እድሜው ውስጥ ከከባድ RSV ለመጠበቅ የቀረበ አዲስ ክትባት። | ከ32 እስከ 36 ሳምንታት እርግዝና ላይ ያሉ ሰዎች። | ጨቅላ ህጻናት በመጀመሪያ የህይወት እድሜያቸው ወቅት ለከባድ RSV ህመም የመጋለጥ ከፍተኛ አደጋ ላይ ናቸው። | በአብዛኛው ከሴፕቴምበር እስከ ጃንዋሪ በሆነው የRSV ወቅት። | የጤና መምሪያዎች፣ ፋርማሲዎች እና የህክምና ጽህፈት ቤቶች። |
| **የRSV የአንቲቦዲ (የበሽታ መከላከያ) ክትባት መስጠት ለጨቅላ ህጻናት** | ጨቅላ ህጻናትን ከከባድ RSV ለመጠበቅ አዲስ የአንቲቦዲ ክትባት መስጠት (ክትባት ያልሆነ)። ይህ የክትባት አሰጣጥ RSVን ለመዋጋት የሰውነትን የበሽታ መከላከል ስርዓት ችሎታን ይገለብጣል (ይኮርጃል)። | ሁሉም ከ 8 ወር በታች የሆኑ ጨቅላ ህጻናት እና ከ 8 እስከ 19 ወር እድሜ ያላቸው ልጆች ለከባድ ህመም የተጋለጡ ናቸው። አብዛኞቹ ጨቅላ ህጻናት ወላጅ እርጉዝ በነበሩበት ጊዜ የRSV ክትባት ከወሰዱ ይህን ክትባት መውሰድ አያስፈልጋቸውም። | ጨቅላ ህጻናት በመጀመሪያ የህይወት እድሜያቸው ወቅት ለከባድ RSV ህመም የመጋለጥ ከፍተኛ አደጋ ላይ ናቸው። | ሴፕቴምበር እና ኦክቶበር ላይ ክትባቱን ማግኘት በጣም ጥሩ ጊዜ ነው፣ ነገር ግን በኋላ ላይ በRSV ወቅት ከተወሰደ አሁንም ጥበቃን ሊያደርግ ይችላል። | የጤና መምሪያዎች፣ ፋርማሲዎች፣ የህክምና ጽህፈት ቤቶች እና የውልደት ሆስፒታሎች። |

**ለበለጠ መረጃ**

ይህንን ይጎብኙ፦ https://www.vdh.virginia.gov/epidemiology/respiratory-diseases-in-virginia/

በበርካታ ኬዞች ውስጥ፣ እነዚህ ክትባቶች በተመሳሳይ ጊዜ ላይ ሊሰጡ ይችላሉ። ስለማንኛውም የበሽታ መከላከያ ክትባት ጥያቄዎች ካሉዎት፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ወይም የፋርማሲ ባለሙያውን ያነጋግሩ። የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ከሌለዎት፣ በ vdh.virginia.gov/health-department-locatorላይ የእርስዎን አካባቢያዊ የጤና መምሪያ ያግኙ እና ያነጋግሯቸው።

*መጨረሻ የዘመነው 09/2023*